ኅብረት ለምርጫ(CECOE)
የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ
Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Elections

# በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአፋር፣ ሶማሌ እና ማዕከላዊ ክልሎች የተካሄደውን ቀሪ እና ድጋሚ ምርጫ የድምፅ አሰጣጥ ሂደት የመጀመሪያ ደረጃ የትዝብት ሪፖርት



ሰኔ 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ (ኅብረት ለምርጫ) ከ175 በላይ ሀገር በቀል የሲቪል ማህበራትን ያቀፈ ኅብረት ነው። ኅብረቱ ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ የዜጎች የምርጫ ታዛቢ ቡድን ሲሆን ዋና ዓላማውም በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉን አቀፍ፣ ግልጽ እና በተጠያቂነት ምርጫዎች እንዲከናወኑ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው።

በ2010 ዓም የተጀመረው የፖለቲካ ማሻሻያ ሂደት የተለያዩ የህግ እና ተቋማዊ ማሻሻያዎችን አድርጓል። ከተካሄዱት ማሻሻያዎች መካከል ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ከመካሄዱ በፊት የምርጫ ሕጉን ማሻሻል፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን እንደገና ማቋቋም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባ ሥርዓትን መከለስ እና አጠቃላይ የምርጫ ሁኔታን ማሻሻል ይገኙበታል። ምንም እንኳ እነዚህ ማሻሻያዎች ቢደረጉም በትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ አማራ እና አፋር ክልሎች የዴሞክራሲ ተሃድሶው ሂደቱን የሚያውኩ ብቻ ሳይሆን ከላይ በተዘረዘሩት ክለሎች በ2013 ዓም በተካሄደውአጠቃላይ ምርጫ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድሩ አፋሳሽ ግጭቶች ተከስተዋል።ከዚህ በተጨማሪም ምርጫ ቦርድ በቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል እና የሶማሌ ክልል አንዳንድ የምርጫ ክልሎች በምርጫ ሂደቱ ላይ በታዩ ከፍተኛ ጉድለቶች ምክንያት የምርጫ ውጤቱን ሰርዟል። በዚህም ምክንያት የተወሰኑ የፌደራል ፓርላማ እና የክልል ምከር ቤቶች መቀመጫዎች ክፍት ሆነው ቆይተዋል።

ስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ ባልተከናወነባቸው አካባቢዎች እና ድጋሚ ምርጫ እንዲከናወንባቸው በቦርዱ ውሳኔ በተሰጠባቸው የምርጫ ክልሎች በተለይም በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ሶማሌ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች ምርጫን ማድራጅት አስፈላጊ በመሆኑ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቀሪ እና ድጋሚ ምርጫዎችን በአራቱ ክልሎች እንደሚያከናውን ማሳወቁ እና ፤በመጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ቦርዱ የቀሪ እና ድጋሚ ምርጫዎች የሚካሄዱበትን የምርጫ የጊዜ ሠሌዳ ለህዝብ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል። በዚህ የጊዜ ሠሌዳ መሰረት ሰኔ 6 ቀን 2016 ዓ.ም የድምጽ መስጫ ቀን እንዲሆን ተወስኖ የነበረ ቢሆንም ቦርዱ የምርጫው ቀን ወደ ሰኔ 09 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲተላለፍ አድርጓል። ነገር ግን ሰኔ 09 ቀን 2016 ዓ.ም ከዋለው የኢድ አል አድሃ ኃይማኖታዊ ክብረ በዓል ጋር በመገጣጠሙ ቦርዱ የድምጽ መስጫ ቀኑን በድጋሚ ወደ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም አዘዋውሮታል። ከምርጫ ቦርድ በተገኘው መረጃ ሰኔ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ለሚካሄዱት ቀሪ እና ድጋሚ ምርጫዎች በአጠቃላይ 1258 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች (ከነዚህ ውስጥ 578 በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ 388 በአፋር፣ 123 በሶማሌ እንዲሁም 169 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች እንደሚያቋቁም ገልጿል።

# የትዝብት ግኝቶች አጭር ማጠቃልያ

ሰኔ 16 ቀን 2024 የተካሄደውን ቀሪ ምርጫ እና ድጋሚ ምርጫ ትዝብት ዋና አላማ በተደራጀ መልኩ የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማቅረብ በምርጫው ሂደት ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነበር። ይህንንም ለማሳካት CECOE በምርጫው ቀን ከቀኑ 5፡30 ላይ በተመደቡበት ምርጫ ጣቢያ የደረሱ ተቅማጭ ታዛቢዎችን አሰማርቷል።

## የምርጫ ቁሳቁሶች መሟላት

የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጽ ከጎደለብት ከሶማሌ ክልል በስተቀር ምርጫ በተካሄደባቸው እና ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎቹን ባሰማራባቸው ክልሎች የሚገኙ የምርጫ ጣቢያወች የትዝብት ግኝቶች የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘታቸውን ያሳያል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከዚህ ቀደም ከነበሩት ተሞክሮዎች ጋር ሲነጻጸር በማነፃፀር የምርጫ ቁሳቁሶችን አሟልቶ በወቅቱ በማቅረብ የሚያስመሰግን ስራ አከናውኗል።

# የምርጫ ጣቢያወች ተደራሽነት

የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎች በምርጫ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ ያበረታታል፣ ክምርጫ ተሳትፎ የሚገለሉ ምራጩችን ይቀንሳል፣ በዚህም የመራጩች ተሳትፎ እንዲጨምር አስተዋጽኦ ያደርጋል። ኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው ክልሎች የትዝብት ግኝቶች እንደሚያሳዩት የምርጫ ጣቢያዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለነፍሰ ጡር እናቶች፣ ህጻናት ላሏቸው ሴቶች እና አረጋውያን ተደራሽ ነበሩ። ይህ መጠቀስ የሚገባው ሌላው አዎንታዊ መሻሻል ነው።

## የምርጫ አስፈፃሚዎች የሥርዓተ-ፆታ ስብጥር እና ብዛት

የምርጫ አስፈጻሚወች ቁጥር እና የምርጫ አስፈጻሚወቹ የስርዓተ-ፆታ ስብጥር ኅብረቱ ታዛቢወቹን ያሰማራባቸው ክልሎች የሚጋሯቸው ጉዳዮች ነበሩ። በየድምጽ መስጫ ጣቢያ የምርጫ እስፈጻሚውች ቁጥር ከሞላ ጎደል አምስት እንዲሆን መደርጉ ክምርጫ ህጉ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ኅብረቱ መታዘብ ችሏል። ከአምስቱ የምርጫ አሰፈጻሚወች መካከል ቢያንስ ሁለቱ ሴቶች መሆናቸውንም የትዝብት ግኝቱ ያመለከታል። ክዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያዎች ሴት የምርጫ አስፈጻሚወች በዋና የምርጫ አስፈጻሚነት ማገልገላቸውንም ኅብረቱ መታዘብ ችሏል። ምንም እንኳ ቢያንስ ሶስት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በየምርጫ ጣቢያው ማሰማራት ህጋዊ ቢሆንም፣ አምስት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በየምርጫ ጣቢያው መሰማራታቸው የምርጫ ህጉ መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ በመሆኑ የሚያስመሰግን ተግባር ነው። መስፈርቱን ወጥነት ባለው መንገድ ማሟላት የምርጫ ህጉን ማክበር ነው። በሌላ በኩል የሴት ዋና ምርጫ ኦስፈጻሚወችን ብዛት ከፍ ለማድረግ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

## መጠለያ

ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መጠለያ መኖር ድምጽ ለመስጠት ወረፋ ይዘው ተራቸወን የሚጠብቁ መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሀይ ለመከላከል ወሳኝ ነገር ነው። የምርጫ ጣቢያዎችን በሚዘጋጅበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው አንዱ እና አስፈላጊው ነገር ቢኖር ወረፋ የሚጠብቁ መራጮች ከፀሐይ እና ከዝናብ የሚጠለሉብት መጠለያ ቦታ አለ ወይ? የሚለው ነው። ዝናባማ በሆነ ወቅት ለሚካሄዱ ምርጫዎች መጠለያ መኖር ይበልጥ አስፈላጊ ነው። ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ መራጮች ዝናቡን ሽሽት ስልፋችውን በትነው በየፊናቸው የመሄድ ዕድላቸው ከፍተኛ ሲሆን በዚህ የተነሳ የመምረጥ መብታቸውን ሳይገለግሉብት ይቀራሉ። በአራቱም ክልሎች የተሰማሩት የ የኅብረቱ ታዛቢዎች አብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች ለመራጮች በቂ መጠለያ እንዳልነበራቸው ገልጸዋል።

## የቅረታ ስሚ ኮሚቴወች

የምርጫ ህጉ ለምርጫ ቦርድ ሶስት አባላት ያሉት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በምርጫ ጣቢያዎች እንዲያቋቁም ስልጣን ሰጥቶታል። ይሁን እንጂ በህጉ መሰረት ከተቋቋሙት ከጅግጅጋ ሁለት ምርጫ ጣቢያዎች (ጅ 06 ምርጫ ጣቢያ 02 እና ጂ 04 ምርጫ ጣቢያ 03) በስተቀር በአብዛኛዎቹ የምርጫ ጣቢያዎች የኅብረቱ ይታዘባችወ ቅሬታን ለመስማት የተቋቋሙት አብዛኛውቹ ኮሚቴዎች አንድም ከምርጫ ህጉ ጋር የማይጣጣሙ ናቸው አለያም ጨርሶ አልተቋቋሙም።

## የምርጫ ቅስቀሳ እና ያልተፈቀደላችው ስወች በምርጫ ጣቢያ ውስጥ መገኘት

የምርጫ ህጉ ከምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ውስጥ ቅስቀሳ ማድረግን በጥብቅ ይከለክላል። በጅግጅጋ በአንድ የምርጫ ጣቢያ (ጂ 09 ምርጫ ጣቢያ-3/ሀ)) ለብልጽግና ፓርቲ የሚቀሰቅሱ ግለሰቦች ከምርጫ ጣቢያው 20 ሜትር ርቀት ላይ ተስተውለዋል። በተመሳሳይ በአፋር ክልል በምርጫ ወቅት ያልተፈቀደላችው ግለሰቦች በተለይም የቀበሌ ባለስልጣናት በ"ገዋንኔ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ጋልኤብ ለ" ምርጫ ጣቢያ ውስጥ ተገኝተዋል።

## የምርጫ ቅስቀሳ እና ያልተፈቀደላችው ስወች በምርጫ ጣቢያ ውስጥ መገኘት

የምርጫ ህጉ ከምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ውስጥ ቅስቀሳ ማድረግን በጥብቅ ይከለክላል። በጅግጅጋ በአንድ የምርጫ ጣቢያ (ጂ 09 ምርጫ ጣቢያ-3/ሀ)) ለብልጽግና ፓርቲ የሚቀሰቅሱ ግለሰቦች ከምርጫ ጣቢያው

20 ሜትር ርቀት ላይ ተስተውለዋል። በተመሳሳይ በአፋር ክልል በምርጫ ወቅት ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች በተለይም የቀበሌ ባለስልጣናት በ"ገዋንኔ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ጋልኤብ ለ" ምርጫ ጣቢያ ውስጥ ተገኝተዋል።

### የማንነት ማረጋገጫ ሳይኖር ድምጽ መስጠት

በአሶሳ ዞን በሚገኙ ሁለት ምርጫ ጣቢያዎች (አሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 03 ሀ 2 እና ቡልደግሉ 01 ምርጫ ጣቢያ ቡልደግሉ ከተማ 01) ስማቸው በመራጭ መዝገብ ላይ ባይገኝም በአካል ጉዳተኝነት እና በእድሜ ምክንያት እንዲመርጡ የተፈቀደላቸው መሆኑን የኅብረቱ የትዝብት ግኝት ያሳያል። ከዚህ በተጨማሪ በምርጫ ህጉ ከተደነገገው አሰራር በተቃራኒ፣ በአፋር ክልል በሚገኝ አንድ የምርጫ ጣቢያ (ገዋንኔ 01 ምርጫ ጣቢያ ጋልኤብሃ) መራጮች የማንነት ማረጋገጫም ሆነ የምስክሮችን ቃል ሳያሰሙ እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል።

### የመራጮች ጣት ላይ የማይለቅ ቀለም አለማድረግ

የምርጫ ህጉ መራጮቸ ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት የመራጮች ጣት በማይለቅ ቀለም እንዲቀልም የሚያስገድድ ቢሆንም በአሶሳ ዞን በሚገኝ አንድ ምርጫ ጣቢያ (አሶሳ 02 ምርጫ ጣቢያ 02 02 ሀ 1ለ) ሰባት መራጮች በጣቶቻቸው ላይ የማይለቅ የጣት ቀለም ሳይደረግላቸው እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል። በተመሳሳይ በአፋር ክልል በሶስት ምርጫ ጣቢያዎች ማለትም በአዋሬ እና ለምለምነን ምርጫ ጣቢያ 1 ግለሰብ፤ ደንቡዲስ፣ ሃዶና ቢዳሪ ምርጫ ጣቢያ 8 ግለሰቦች እንዲሁም ሃዶ እና ከልዋን 01 ምርጫ ጣቢያ ከልዋን ከተማ 6 ግለሰቦች ጣቶቻቸውን በማይለቅ ቀለም ሳይቅልም አእንዲመርጡ ተደርጓል።

### የድምጽ ቆጠራ መቋረጥ

አሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 03 ሀ 2፣ አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ሀ 2A፣ አሶሳ 02 ምርጫ ጣቢያ 02 02 ሀ 1B፣ እና አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ለ 2 ፈንቲግራሩ ምርጫ ጣቢያ ጉለሊ በምርጫ ቦርድ የተሰጠው የድምጽ አስጣጡ እስከ ምሽቱ 2 ሰአት መራዝሙን የተሰጠው መግለጫ ዘግየተው በመስማታቸው ፤የድምፅ ቆጠራው በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች እንዲቆም አድርጓል። የጣቢያዎቹን ስም ለመግለፅ ያክል ፤አሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 03 ሀ 2፣ አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ሀ 2A፣ አሶሳ 02 ምርጫ ጣቢያ 02 02 ሀ 1B፣ and አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ለ 2ፈንቲግራሩ ምርጫ ጣቢያ ጉለሊ።

## ቤንሻንጉል ጉሙዝ

ኅብረት ለምርጫ በሎጂስቲክ እና ኦፐሬሽኝ ችግር የተነሳ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በድምጽ መስጫ ቀን በአሶሳ ዞን ብቻ ታዛቢዎቹን ያሰማራ ሲሆን በቀሩት ሁለት ዞኖች ማለትም በመተከል እና በካማሺ ዞኖች ታዛቢዎቹን ማሰማራት ሳይችል ቀርቷል። ስለሆነም ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት በአሶሳ ዞን በ20 የምርጫ ጣቢያዎች ተሰማርተው ቀኑን ሙሉ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ሲታዘቡ በነበሩ 20 ታዛቢዎች አማካኝነት በተሰበሰበው የትዝብት መረጃ ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ሲሆን ኅብረት ታዛቢውችን ለማሰማራት የተከተለው አመችነትን መሰረት ያደርገ የስመሪት ዘዴን (convenient deployment method) በመጠቀም ነበር። ይህ ሪፖርት ያካተተው የምርጫ አስፈጻሚዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን፤ የምርጫ ጣቢያዎች ዝግጅትን፤ የድምጽ መሰጫ ጣቢያ አከፋፈትን ፤ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን ፤ ፤የድምጽ መሰጫ ጣቢያ መዘጋት፣ ቆጠራ እና የውጤት ማዳመርን እንዲሁም በድምጽ ምስጫ ጣቢያ ውጤት ምለጥፍን/ የሚምለከቱ መረጃዎችን ይዟል።

## ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ

1. የምርጫ አስፈጻሚዎች የድምጽ መስጫ ጣቢያው ከመከፈቱ ከንጋቱ 12:00 ሰዓት በፊት በምርጫ ጣቢያው መገኘት ይጠበቅባቸዋል። በ19 የምርጫ ጣቢያውች የምርጫ አስፈጻሚዎች ከማለዳ 11:30 ላይ በምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተዋል።

2. በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች፣ የተስማሩ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተገኝተው እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።

3. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 12:00 ሰአት መከፈት አለባቸው። የኅብረቱ ታዛቢዎች ከማለዳው 12 ሰዓት በ18 የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ መጀመሩን ሲያመለክቱ በተቀሩት 2 ምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ከጠዋቱ 1 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው ግዜ መጀመሩን ገልጸዋል።

4. የምርጫ ህጉ በወታደራዊ ካምፖች፣ በግል መኖሪያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሀይማኖት ተቋማት ህንጻዎች፣ የጤና ተቋማት፣ የመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ውስጥ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ይከለክላል። በዚህ መሠረት የኅብረቱ ታዛቢውች የታዘቧቸው ሁሉም( 20) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ሕጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች ፣መቋቋማቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. በምርጫ ቀን የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ፣ የምርጫ ህጉ በምርጫ ጣቢያው ውስጥም ሆነ ከምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ላይ ማንኛውንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎችን በግልፅ ይከለክላል። ከዚህ ጋር በተያያዝ በ20ውም የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች ሪፖርት አልተደረገም።

## የምርጫ ጣቢያዎች ዝግጅት

1. የምርጫ ጣቢያዎች የሚቋቋሙበት ቦታ ለዜጎች ያላቸው ተደራሽነት ዜጎች በምርጫ ሂደቱ በሚኖራቸው ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ አለው። በዚህ ረገድ 14 የምርጫ ጣቢያዎች በድንኳን ውስጥ ሲቋቋሙ 4 በህንፃዎች እና 2 በቆርቆሮ ወይም በዛፍ ሰር መቋቋማችወን በኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት ተደርጓል።

2. መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሐይ ወረፋ ለመከላከል ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መጠለያ መኖሩ በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ውስጥ አስፈላጊ ትግበር ነው። በዚህ ረገድ 7 የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች የነበሯቸው ሲሆን ፤ 13 የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሀይ የሚከላከሉ መጠለያዎች አልነበሯቸውም።

3. በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ሌላው ወሳኝ ጉዳይ አረጋውያን፣ ነፍሰ ጡር ሴቶቸን፤ ህጻናትን አስከተለው ለሚመጡ እናቶች እና አካል ጉዳተኞችን ለመሳሰሉ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት ጋር የተያያዘ ሲሆነ 14 የምርጫ ጣቢያዎች ከዚህ በላይ ለተዘረዘሩት የህብረተብ ክፍሎች ተደራሽ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 6 ምርጫ ጣቢያዎች ግን ተደራሽ አልነበሩም።

4. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎችን በተሟላ መንገድ ለማዘጋጀት የምርጫ ቁሳቁሶች ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘት አስፈላጊ ነገር ነው። የደምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ ኦፊሴላዊ የምርጫ ቦርድ ማህተም ፣ የውጤት እና የእርቅ ቅጽ፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምጽ

መስጫ ሳጥን፣ እና የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች በምርጫ ጣቢያዎች ተሟልተው ይገኙ እንደሆነ የተጠየቁት ጎብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በታዘቧቸው ሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘታቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን እንዲያሳይ ያስገድዳል። በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊወች የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ እንደነበሩ አሳይቷል።

6. የምርጫ ህጉ ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈጻሚዎች በየምርጫ ጣቢያዎቹ መገኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። ጎብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ 5 የምርጫ አስፈጻሚዎች መገኘታቸውን ከነዚህም መካከል በአማካይ 2 የምርጫ አስፈጻሚዎች ሴቶች እንደነበሩ ሪፖርት አድርገዋል። የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎችን የሥርዓተ-ፆታ ውክልናን በተመለከተ በ3 የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎቹ ሴቶች ሲሆኑ በቀሪዎቹ 17 የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎቹ ወንዶች እንደነበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ጎብረቱ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች አንድም አካል ጉዳተኛ የምርጫ አስፈጻሚ አለመኖሩን አረጋግጧል።

7. የምርጫ ህጉ ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በምርጫ ጣቢያዎች እንድሚድያቋቁም ይደነግጋል። በዚሁ መሰረት በ2 የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የተቋቋሙ ሲሆን በአንዳንድ የምርጫ ጣቢያውች የምርጫ ህጉ ከሚደነግገው ውጭ መቋቋማቸውን፤በአብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ጨርሶ አለመቋቋማችወን የተገዘብት ያመለክታል።

8. የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኘታቸውን በተመለከተ፣ በ18 የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ውኪሎች መግኘታቸውን ታዛቢዎች ገልጸዋል።

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደት

1. በሁሉም (20) የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ታዛቢዎች ጣቢያዎቹን ለቀው እንዲወጡ አለመጠየቃቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

2. የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን፣ አቅመ ደካሞችን፣ እርጉዝ ሴቶችን፣ እና ህጻናትን የያዙ ወላጆች በ19 የምርጫ ጣቢያዎች ቅድሚያ የስጡ ሲሆን በ1 የምርጫ ጣቢያ ግን ቅድሚያ እንዳልተሰጣቸው ታዛቢውች ግልጸዋል።

3. አካል ጉዳተኞች በ10 የምርጫ ጣቢያዎች በመረጡት የግል ረዳት እግዛ እንዲደረግላቸው የተፈቀደላቸው ሲሆን በ10 የምርጫ ጣቢያዎች ማንም መራጭ እርዳታ አላስፈለገውም ነበር።

4. የምርጫ ህጉ መራጮች ለመመዝገብ እና/ወይም ድምጽ ለመስጠት የማንነት ማረጋገጫ እና/ የመኖሪያ ማረጋገጫ እንዲያሳዩ ያስገድዳል። ማንነታቸውን እና የመኖሪያ ቦታቸውን ማረጋገጥ ያልቻሉ መራጮች በድምጽ አሰጣጡ ሂደት እንዳይሳተፉ ህግ ይከለክላል። ነገር ግን የምርጫ ህጉ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሲከስቱ ማንነታችውን በምስክሮች እንዲያረጋግጡ ህጉ ይፈቅዳል። በዚሁ መሰረት በ14 የምርጫ ጣቢያዎች የማንነት ማረጋገጫ እና/ወይም የነዋሪነት ማረጋገጫ ያላቀረቡ መራጮች አስምስከረው ድምጽ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል። በቀሪዎቹ 6 ምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም መራጮች ማንነታቸውን እና መኖሪያቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይዘው መጥተዋል።

5. በተቃራኒው አንዳንድ መራጮች "አሶሳ 03 ጣቢያ 03 03 ምርጫ ሀ 2 እና "አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ሀ 2A" በተባሉ ሁለት የምርጫ ጣቢያዎች የማንነት ማረጋገጫ እና ነዋሪነታቸውን ቢያረጋገጡም እንዳይመርጡ ተደርገዋል። በእነዚህ ምርጫ ጣቢያዎች አንዳንድ መራጮች ስማቸው በመራጭ መዝገብ ላይ አልተገኘም በሚል ድምጽ እንዳይሰጡ ተከልክለዋል። ምርጫው እስከ ምሽት 2 ሰዓት መራዘሙን የ ምርጫ ቦርድ ቢያስታውቅም ከቀኑ 12፡00 ሰዓት በኋላ ወደ ምርጫ ጣቢያው የገቡ ስድስት መራጮች እንዳይመርጡ ተደርገዋል።

6. የምርጫ ህጉ ምራጮች ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት የመራጮች ጣት በማይለቅ ቀለም እንዲቀልም ያስገድዳል። በ19 የምርጫ ጣቢያዎች መራጮች በጣታቸው ላይ የማይለቅ ቀለም ምልክት የተደረገባቸው ሲሆን በአንድ ምርጫ ጣቢያ "አሶሳ 02 ምርጫ ጣቢያ 02 02 ሀ 1B" 7 መራጮች የማይለቅ ቀለም በጣታቸው ላይ አልተደረገም።

7. በምርጫ አዋጁ መሰረት የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የመራጮች ስም በመራጭ መዝገብ ውስጥ መገኘቱን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። ከህጉ በተቃራኒ በምርጫ ጣቢያ "አሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 03 ሀ 2" 1 ግለሰብ እንዲሁም "ቡልደገሉ 01 ምርጫ ጣቢያ ቡልደጋሉ ከተማ 01" ምርጫ ጣቢያ 6 ግለሰቦች አካል ጉዳተኞች ወይም አዛውንቶች ናቸው በሚል ሰቡብ ስማቸው በመራጮች መዝገብ ሳይኖር እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል።

8. የምርጫ ህጉ የምርጫ አስፈጻሚወች ሁሉንም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት ማህተም እንዲያደርጉ ያስገድዳል። የኅብረቱ ታዛቢዎች በታዘቧቸው በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች፣ የምርጫ አስፈጻሚዎች በሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ማህተም ማድረጋቸውን ታዝበዋል።

9. በሁሉም 20 የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ምስጢራዊነት ቀኑን ሙሉ ተከብሮ ነበር።

10. በሁሉም 20 የምርጫ ጣቢያዎች የሚይታይ/ ግልጽ ያልሆነ የአካል ጉዳት ያለባቸው እና አረጋውያን ያልሆኑ መራጮች እርዳታ/ደጋፍ አልተደረገላቸውም ።

11. በድምጽ አሰጣጥ ሂደት በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች ያልተፈቀደላቸው ሰዎች በምርጫ ጣቢያወቹ ውስጥ አልተገኙም።

12. ኅብረቱ በታዘባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በአጠቃላይ ማስፈራራት እና እንግልት በተለይም ድሞ ሴት መራጮች፣ የፓርቲ ውኪሎቸ፤ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈጻሚወች የጥቃት ሰለባዎች አልነበሩም።

13. ቀኑን ሙሉ በሁሉም (20) የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ አልተቋረጠም።

14. የምርጫ አዋጁ የምርጫ ጣቢያዎች የመዝጊያ ሰአት ከቀኑ12፡00 ሰዓት መሆኑን ይደነግጋል። ሰኔ 16 ቀን 2023 የምርጫ ቦርድ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የምርጫ ጣቢያዎች የመዝጊያ ጊዜ ለተጨማሪ ሁለት ሰዓታት ማለትም እስከ ምሽቱ 2፡00 ሰዓት ድረስ መራዘሙን አስታውቋል። የኅብረቱ ታዛቢውች 17 ምርጫ ጣቢያዎች ከቀኑ 12፡00 ሰአት መዝጋታቸወን ሪፖርት ያደርጉ ሲሆን 3 ምርጫ ጣቢያዎች ከምሽቱ 2፡00 ሰአት ላይ መዝጋታችወን ሪፖርት አድርገዋል።

15. ከቀኑ 12፡00 ሰዓት ላይ በምርጫ ጣቢያው መዝጊያ ሰልፍ ላይ የነበሩ ሁሉም መራጮች በህጉ መሰረት የመረጡ ሲሆን በ2 የምርጫ ቦጣቢያወች መራጮቸ 12፡00 ሰዓት በኋላ ድምጽ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።

## የድምጽ ቆጠራ

1. በድምጽ ቆጠራ ወቅት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ ታዛቢዎች ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጡ አልተጠየቁም።

2. የድምፅ ቆጠራ በምርጫው ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መከናወን አለበት። በዚህ መሰረት . የድምጽ ቆጠራው በድምጽ መስጫው እለት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ተካሂዷል።

3. ምርጫ ቦርድ የድምጽ አሰጣጥ ሂደት እስከ ምሽቱ 2 ሰአት እንዲራዘም ያስለፍው ውሣኔ ዘግይቶ በመሰማቱ በ4 የምርጫ ጣቢያዎች (አሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 03 ሀ 2፣ አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ሀ 2A፣ አሶሳ 02 ምርጫ ጣቢያ 02 02 ሀ 1B እና አሶሳ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ለ 2 ፊንቲግራሩ ምርጫ ጣቢያ ጉጉሊ) የድምጽ ቆጠራው ተቋርጧል።

4. በቆጠራው ሂደት በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት ጣልቃገብነት፣ ትንኮሳ እና/ወይም ማስፈራራት አልነበረም።

5. በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ የነበሩ ሃላፊወች በድምጽ ቆጠራው ወቅት የምርጫ ወረቀቶቹን በግልፅ አሳይተዋል።

6. በአንድ የምርጫ ጣቢያ የጣቢያው ሃላፊ ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላችወን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ተመሳሳይ መስፈርቶችን አለመተግበራችውን የትዝብት ሪፖርቱ ያሳያል። ይሀ ክስተት የተከሰተው አሶሳ 03 ምርጫ ጣቢያ 03 03 ሀ 2 በምርጫ ጣቢያ ሲሆን የጣቢያው ሃላፊ ውድቅ መሆን የነበረባቸውን የምርጫ ካርዶች ዋጋ ያላቸው አድርገው ሲያረጋግጡ ተስተውለዋል።

7. ምንም እንኳ ታዛቢዎች ዜጎች ቅሬታቸውን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሲገልጹ ሰምተናል ቢሉም በምርጫ ጣቢያ ለተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የቀረቡ መደበኛ ቅሬታዎች አልነበሩም ።

# አፋር

ይህ ዘገባ የተመጣጠነ የስምሪት ዘዴን/proportional deployment methodology/ በመጠቀም ብምርጫው እለት በ37 የምርጫ ጣቢያዎች በተሰማሩ 37 የሀብረቱ የአጭረ ግዜ /ተቀማጭ ታዛቢዎች አማካኝነት ተሰብስቦ ሪፖርት በተደረግ መረጃ ላይ የተመሰረተ ነው።። ሪፖርቱ የምርጫ አስፈጻሚወች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን፤ የምርጫ ጣቢያዎች ዝግጅትን፤ የድምጽ መሰጫ ጣቢያ አከፋፈትን ፤ የድምጽ አሰጣጥ ሂድተን ፤ ፣የድምጽ መሰጫ ጣቢያ መዘጋትን፣ ቆጠራ እና የውጤት ማዳመርን እንዲሁም በድምጽ ምስጫ ጣቢያ ውጤቱን መለጥፍን/ የሚምለከቱ መረጃዎችን አካትቷል።

## ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ

1. የምርጫ አስፈጻሚውች የድምጽ መስጫ ጣቢያው ከንጋቱ 12:00 ሰዓት ከመክፈቱ አስቅድሞ በምርጫ ጣቢያው መገኘት ይጠበቅባችዋል። በ 34(92%) የምርጫ ጣቢያውች የምርጫ አስፈጻሚውች ከ ማለዳው 11:30 በምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተዋል።

2. በ 37 (100%)) የምርጫ ጣቢያዎች፣ የተስማሩ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተገኝተው እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።

3. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 12፡00 ሰአት መከፈት አለባቸው። የጎብረቱ ታዛቢዎች ከማለዳው 12 ሰዓት እስከ ጠዋቱ 1 ሰዓት ባለው ግዜ በ 37 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ መጀመሩን አመልክተዋል። ያመለከታል።

4. የምርጫ ህጉ በወታደራዊ ካምፖች፣ በግል መኖሪያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ የሀይማኖት ተቋማት ህንጻዎች፣ የጤና ተቋማት፣ የመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ውሰጥ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ይከለክላል። በዚህ መሠረት የጎብረቱ ታዛቢውች 37 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ሕጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች ፣መቋቋማቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. በምርጫ ቀን የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ፣ የምርጫ ህጉ በምርጫ ጣቢያው ውስጥም ሆነ ከምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ላይ ማንኛውንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎችን በግልፅ ይከለክላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ታዛቢውች በ37 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት የምርጫ ዘመቻ/ቅስቀሳ አለመደረጉን ሪፖርት አድርገዋል።

## የምርጫ ጣቢያዎች ዝግጅት

1. የምርጫ ጣቢያዎች የሚቋቋሙበት ቦታ ለዜጎች ያላቸው ተደራሽነት በምርጫ ሂደቱ ዜጎች በሚኖራቸው ተሳተፎ ላይ ተፅእኖ አለው። . በዚህ ረገድ 23 ( 62%) የምርጫ ታቢያወች በድንኳን ውስጥ የተቋቋሙ ሲሆን 4 (11%) በህንፃዎች እና 10 (27%) የምርጫ ጣቢያዎች በዛፍ ወይም በሳር እና በሸራ በተሠሩ መጠለያዮዎች ውስጥ መቋቋማችወን በጎብረቱ ታዛቢውች ሪፖርት ተደርጓል።

2. መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሐይ ለመከላከል ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መጠለያ መኖሩ በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ውስጥ አስፈላጊ ነገር ነው። በዚህ ረገድ በ 12 (32%) የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች ነበሯቸው ፣ 25 (68%) የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሐይ የሚከላከሉ መጠለያዎች አልነበሯቸውም።

3. በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ሌላው ወሳኝ ጉዳይ አረጋውያን፣ ነፍሰ ጡር ሴቶቸን፤ ህጻናትን አስከተለው ለሚመጡ እናቶች እና አካል ጉዳተኞችን ለመሳሰሉ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት ጋር የተያያዘ ሲሆን 24 (65%) የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽ ሲሆኑ 35% (13) የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽ አልነበሩም።

4. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎችን በተሟላ መነገድ ለማዘጋጀት የምርጫ ቁሳቁሶች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘት አስፈላጊ ነገር ነው.። የደምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ኦፊሴላዊ የምርጫ ቦርድ ማህተም ፣ የውጤት እና የእርቅ ቅጽ፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን፣ እና የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች በምርጫ ጣቢያዎች ተሟልተው ይገኙ እንደሆነ የተጠየቁት ጎብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በታዘቧቸው የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም የምርጫ ቁሳቁሶችከ በ37 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኝታቸውን ሪፖርተ አድርገዋል።

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን እንዲያሳይ የምርጫ ህጉ ያስገድዳል። በ 37 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊወች የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ እንደነበሩ አሳይተዋል።

6. በምርጫ ህጉ ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈጻሚውች በየምርጫ ጣቢያዎቹ መገኘት እንዳለባቸው ይደነገጋል። ጎብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ 5 የምርጫ አስፈጻሚወች መገኘታችወን፤

በ6 (16 %) የምርጫ ጣቢያዎች ሴቶች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ሲሆኑ፡በ31 ( 84% ) የ ምርጫ ጣቢያዎች ወንድ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች እንደነብሩ ታዛቢወች ሪፖርት አድርገዋል። ። ከዚህ በተጨማሪ በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ከምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች መካከል አካል ጉዳተኞች አለምኖራቸው በታዛቢወች ሪፖርት ተደርጓል።

7. የምርጫ ህጉ ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በምርጫ ጣቢያዎች እንድሚድያቋቁሙ ይደነግጋል። በዚሁ መሰረት በ በ 14 (38%) የምርጫ ጣቢያዎች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የተቋቋሙ ሲሆን ኮሚቴዎቹ በ23 (62%)ይ የምርጫ ጣቢያዎች አለመቋቋማቸውን የትዝብት ሪፖርቱ ያመልከታል።

8. የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኝታቸውን በተመለከተ በ 29(78%) የምረጫ ጣቢያወች የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች መገኘታቸውን ፤ በ 8 (22%) የምርጫ ጣቢያዎች ግን የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች አለምገኘታቸወን ታዛቢዎች ገልጸዋል።

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደት

1. በ 37(100 %) ድምጽ መስጫ ጣቢያወች በድምጽ አሰጣጥ ሂደተ ታዛቢዎች ጣቢያዎቹን ለቀው እንዲወጡ አለመጠየቃቸውን ታዛቢወች ሪፖርት አድርገዋል

2. የድምጽ መስጫ ጣቢያ ሃላፊዎች ለአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያንን፣ አቅመ ደካሞችን፣ እርጉዝ ሴቶችን፣ እና ህጻናትን ለያዙ ወላጆች በ36 (97%) የምርጫ ጣቢያዎች ቅድሚያ ሰጥተዋል። ነገር ግን በ1 (3%) የምርጫ ጣቢያ ቅድሚያ እንዳልተሰጣቸው ታዛቢወች ሪፖርት አእድርገዋል።

3. አካል ጉዳተኞች በ 32 (86%) የምርጫ ጣቢያዎች የመረጡት የግል ረዳት እንዲረዳቸው የተፈቀደላቸው ሲሆን በ 5 (14$%) የምርጫ ጣቢያዎች ግን ምንም እርዳታ አላስፈለጋቸውም። ሆኖም ፈንጢግራሩ ምርጫ ጣቢያ ጉለሊ በሚባል አንድ የምርጫ ጣቢያ አንድ ሰው ረዳት ለሚሹ መራጮች ደጋግሞ ይረዳ እንደነበር ታዛቢውች ሪፖርት አድርገዋል።

4. የምርጫ ህጉ መራጮች ለመመዝገብ እና/ወይም ድምጽ ለመስጠት የነዋሪንት እና የማንነት ማረጋገጫ እንዲያሳዩ ያስገድዳል። ማንነታቸውን እና የመኖሪያ ቦታቸውን ማረጋገጥ ያለቻሉ መራጮች በድምጽ አሰጣጡ ሂደት እንዲሳተፉ ህጉ አይፈቀደም። ነገር ግን የምርጫ ህጉ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሲክስቱ መራጮች ማንንታችወን በምስክሮች እንዲያረጋግጡ ህጉ ይፈቅዳል። ከዚህ በተቃራኒ በአንድ የምርጫ ጣቢያ “ጓዋንኔ 01 ምርጫ ጣቢያ ጋልኤብሃ” የማንነት ማረጋገጫ እና/ወይም የነዋሪነት ማርጋገጫ ማቅረብ ያልቻሉ መራጮች ሳያስመሰከሩ እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል። በቀሪዎቹ 36(97.29) የምርጫ ጣቢያዎች የማንነት እና የነዋሪነት ማርጋገጫ ያቀረቡ መራጮች በሙሉ ድምጽ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።

5. በምርጫ አዋጁ መሰረት የተመዘገቡ እና የማንነት እና የነዋሪንተ ማረጋገጫ ያቀርቡ መራጮች ድምጽ መስጠት አለባቸው። በዚህ መሰረት በ 37 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም ብቁ መራጮች እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል.።

6. የምርጫ ህጉ ለመመዝገብ እና ድምጽ ለመስጠት ከመፈቀዱ በፊት በመራጮች ጣት ላይ የማይለቅ ቀልም እንዲቀባ ያስገድዳል። በ 34 (92%) የምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ በሁሉም መራጮች ጣት ላይ የማይለቅ ቀለም የተደረገባቸው ሲሆን በሶስት የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ የማይለቅ ቀለም በጣታቸው ላይ የማይለቅ ቀለም ሳይደረግ ድምጽ እንዲሰጡ ተደርጓል። አዋሬ ና ለምለምነን ምርጫ ጣቢያ ፤ ደንገበዲስ, ሃዶና ቢዳሪ

ምርጫ ጣቢያ ሃዶ እና and ከልዋን 01 ምርጫ ጣቢያ ከልዋን ከተማ 11,8 እና 6 ግለሰቦች እንደየቅደም ተከተላቸው , በጣቶቻቸው ላይ የማይለቅ ቀለም ምልክት ሳይደረግባቸው ድምጽ ሰጥተዋል::

7. በምርጫ አዋጁ መሰረት የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የመራጮች ስም በመራጭ መዝገብ ውስጥ መገኘቱን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። ከህጉ በተቃራኒ በአንድ የምርጫ ጣቢያ "ገዋኔ 01 ምርጫ ጣቢያ ገልሀ_1" አምስት ግለሰቦች በመራጮች መዝገብ ላይ ስማቸወ ሳይገኙ እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል።

8. የምርጫ ህጉ የምርጫ አስፈጻሚወች ሁሉንም የድምጽ መስጫ ወርቀቶች ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት ማህተም እንዲያደርጉ ያስገድዳል። የኅብረቱ ታዛቢወች በታዘቧቸው በሁሉም37 (በ100 %) የምርጫ ጣቢያዎች፣ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች ሁሉንም የምርጫ ወረቀቶችን ማህተም አድርገውባቸዋል።

9. በምርጫ ጣቢያዎች 37(100%) የድምፅ ምስጢራዊነት ቀኑን ሙሉ ተከብሮ ነበር።

10. በ 37 (100) የምርጫ ጣቢያ የሚታይ የአካል ጉዳት የሌላባቸው እና አረጋውያን ያልሆኑ መራጮች ደጋፍ አልተደረገላቸውም።

11. በድምጽ አሰጣጥ ወቅት፣ "ገዋንኔ 01 ምርጫ ጣቢያ 01 ጋልኤብ ለ" ምርጫ ጣቢያ ውስጥ ያልተፈቀለደለት ሰው ማለተም የቀበሌ ባለስልጣን ተገኝቷል።

12. ኅብረቱ በታዘባቸው 537(100%) የምርጫ ጣቢያዎች የማስፈራራት እና እንግልት በአጠቃላይ በተለይም ደ'ም ሴት መራጮች፣ የፓርቲ ውኪሎቸን፤፣ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈጻሚወች የጥቃት ሰለባዎች አልነበሩም።

13. በ 37 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ቀኑን ሙሉ አልተቋረጠም።

14. የምርጫ አዋጁ የምርጫ ጣቢያዎች የመዝጊያ ስአት ከቀኑ12፡00 ሰዓት መሆኑን ይደነግጋል። በምርጫ ህጉ መሰረት በ 37(100%) የምርጫ ጣቢያዎች ከቀኑ 1200 ሰአት ላይ የምርጫ ጣቢያውች ተዘግተዋል።

15. በምርጫ ጣቢያው መዝጊያ ከቀኑ 12፡00 ሰዓት ላይ ብ 18 (35%) የምርጫ ጣቢያወች ሰልፍ ላይ የነበሩ መራጮች እንዲመርጡ ተፈቅዶላቸዋል። በ 24 (65%) የምርጫ ጣቢያዎች መዝጊያ ላይ ሰልፍ ላይ የነበሩ መራጮች አልነበሩም.

## የድምጽ ቆጠራ

1. በድምጽ ቆጠራ ወቅት በ37 (100% (37) ምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ ታዛቢዎች ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጡ አልተጠየቁም።

2. የድምፅ ቆጠራ በምርጫው ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መከናወን አለበት።. በ 37 (100%)) የምርጫ ጣቢያዎች ቆጠራው በድምጽ መስጫ ቀን በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ተካሂዷል።

3. በ 37 ( 100% ) የምርጫ ጣቢያዎች ቆጠራው አልተቋረጠም።

4. በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በቆጠራው ሂደት ምንም አይነት ጣልቃገብነት፣ ትንኮሳ እና/ወይም ማስፈራራት አልነበረም።

5. በሁሉም /በ 37 (100%) ምርጫ ጣቢያዎች የነበሩ ሃላፊወች በድምጽ ቆጠራው ወቅት የድምጽ መስጫ ወረቀቶቹን በግልፅ አሳይተዋል።

6. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በ 37 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸወን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ተመሳሳይወይም /ወጥ መመዘኛዎችን ተጠቅመዋል"።

7. ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበ ምንም አይነት መደበኛ ቅሬታ እንደሌለ ታዛቢዎች ቢናገሩም ዜጎች ቅሬታቸውን ለምርጫ ጣቢያው ኃላፊ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሲገልጹ ሰምተናል ብለዋል።

# ማዕከላዊ ኢትዮጵያ

ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት በማዕከላዊ ኢትዮጵያ መስቃን እና ማረቆ የምርጫ ክልል በ12 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ተሰማርተው ቀኑን ሙሉ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ሲታዘቡ በነበሩ 12 ታዛቢዎች አማካኝነት በተሰበሰበው የትዝብት መረጃን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ሲሆን ታዛቢዎቹን ለማስማራት ኅብረቱ ተመጣጣኝ የስምሪት ዘዴን (proportional deployment method) ተጠቅበሟል። ሪፖርቱ የምርጫ አስፈጻሚዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስን፤ የምርጫ ጣቢያዎች ዝግጅትን፤ የድምጽ መሰጫ ጣቢያ አከፋፈትን ፤ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን ፣የድምጽ መሰጫ ጣቢያ መዘጋትን፣ ቆጠራ እና የውጤት ማዳመርን እንዲሁም በድምጽ መስጫ ጣቢያ ውጤት መለጠፍን አ/ የሚመለከቱ መረጃዎች አካትቷል።

## ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ

1. የምርጫ አስፈጻሚዎች ች ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት ጣቢያዎቹ ከመከፈታቸው አስቀድሞ በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት ይኖርባቸዋል። በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች ከ ማለዳው 11፡30 በምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተዋል።

2. በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የተሰማሩ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተገኝተው እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።

3. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 12፡00 ሰአት መከፈት አለባቸው። የኅብረቱ ታዛቢዎች ከማለዳው 12 ሰዓት በ 11 (92%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ መጀመሩን አመልክተዋል። ነገር ግን በአንድ (1) የምርጫ ጣቢያ ***"1 ምርጫ ጣቢያ ቆሼ 32ኛ ክ/ጦር ብርጌድ 2"*** ከንጋቱ 12 ሰዓት በፊት የድመጽ መስጠት ሂደት ተጀምሮ ነበር።

4. የምርጫ ህጉ በወታደራዊ ካምፖች፣ በግል መኖሪያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ የኃይማኖት ተቋማት ህንጻዎች፣ የጤና ተቋማት፣ የመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ውሰጥ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋምን ይከለክላል። በዚህ መሠረት የኅብረቱ ታዛቢዎች በታዘቧቸው በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ሕጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች ፣መቋቋማቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. በምርጫ ቀን የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ፣ የምርጫ ህጉ በምርጫ ጣቢያው ውስጥም ሆነ ከምርጫ ጣቢያዎች 200 ሜትር ርቀት ላይ ማንኛውንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎችን በግልፅ ይከለክላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች ሪፖርት አልተደረገም።

## የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ዝግጅት

1. የምርጫ ጣቢያዎች የሚቋቋሙበት ቦታ ለዜጎች ያላቸውን ተደራሽነት ዜጎች በምርጫ ሂደቱ በሚኖራቸው ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ አለው። በዚህ ረግድ በ 10 (83%) የምርጫ ጣቢያዎች በድንኳን ውስጥ ሲቋቋሙ1 ( 8 %) በህንፃዎች እንዲሁም 1 (8%) በቆርቆሮ ወይም በዛፍ ሰር መቋቋማቸውን በኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት ተደርጓል።

2. መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሐይ ለመከላከል ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መጠለያ መኖሩ በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ውስጥ አስፈላጊ ነገር ነው። በ 3 (25%) የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች የነበሯቸው ሲሆን ፤ በ 9 (75 %) የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሀይ የሚከላከሉ መጠለያዎች አልነበሯቸውም።

3. በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ሌላው ወሳኝ ጉዳይ አረጋውያን፣ ነፍሰ ጡር ሴቶቸን፤ ህጻናትን አስከተለው ለሚመጡ እናቶች እና አካል ጉዳተኞችን ለመሳሰሉ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት ጋር የተያያዘ ሲሆን በ 12 (100 %) የምርጫ ጣቢያዎች ክዚህ በላይ ለተዘረዘሩት የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ ነበሩ።

4. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎችን በተሟላ መነገድ ለማዘጋጀት የምርጫ ቁሳቁሶች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘት አስፈላጊ ነገር ነው። የደምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ኦፊሴላዊ ምርጫ ቦርድ ማህተም ፣ የውጤት እና የእርቅ ፎርም፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን እና የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች በምርጫ ጣቢያዎች ተሟልተው ይገኙ እንደሆነ የተጠየቁት ኅብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በታዘቧችው በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉም የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኝታቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን እንዲያሳይ የመርጫ ህጉ ያስገድዳል። በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ ምሆናችወን አሳይተዋል።

6. የርጫ ህጉ ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈጻሚዎች በየምርጫ ጣቢያዎቹ መገኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። ኅብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ 5 የምርጫ አስፈጻሚዎች መገኘታቸውን ከነዚህም መካከል በአማካይ 2 የምርጫ አስፈጻሚዎች ሴቶች እንደነበሩ ሪፖርት አድርገዋል። የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎችን የሥርዓተ-ፆታ ውክልናን በተመለከተ በ4 (33 %) የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎቹ ሴቶች ፤ በቀሪዎቹ 8 (67%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎቹ ወንዶች እንደነበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ኅብረቱ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች አንድም አካል ጉዳተኛ የምርጫ አስፈጻሚ አለመኖሩን አረጋግጠዋል።

7. የምርጫ ህጉ ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በምርጫ ጣቢያዎች እንድሚድያቋቁም ይደነግጋል። በዚሁ መሰረት በ 3 (25%) የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የተቋቋሙ ሲሆን በ 9 (75 %) የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ኮሚቴዎቹ አልተቋቋሙም።

8. የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኝታቸውን በተመለከተ፣ በ 8 (67%) የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ውኪሎች መግኝታቸውን ታዛቢዎች የገለጹ ሲሆን በ 4 (33%) የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች አለመገኘታችወን ታዛቢወች አእመልክተዋል።

# የድምጽ አሰጣጥ ሂደት

1. በ 12 (100%) የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ታዛቢዎች ጣቢያዎቹን ለቀው እንዲወጡ አለመጠየቃቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

2. አካል ጉዳተኞችን፣ አረጋውያንን፣ አቅመ ደካሞችን፣ እርጉዝ ሴቶችን፣ እና ህጻናትን የያዙ ወላጆች በ12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች ቅድሚያ የተሰጣቸው መሆኑን ታዛቢዎች ገልጸዋል።

3. አካል ጉዳተኞች በ 8(67%) በመቶ የምርጫ ጣቢያዎች በመረጡት የግል ረዳት እግዛ እንዲደረግላችው የተፈቀደላቸው ሲሆን በ 4 (33 %) የምርጫ ጣቢያዎች የትኛውም መራጭ እርዳታ አላስፈለገውም ነበር። በተጨማሪም፣ እርዳታ የሚሹ መራጮችን በተደጋጋሚ የረዱ መራጮች አልነበሩም።

4. የምርጫ ህጉ መራጮች ለመመዝገብ እና/ወይም ድምጽ ለመስጠት የነዋሪነት እና የማንነት ማረጋገጫ እንዲያሳዩ ያስገድዳል። ማንነታቸውን እና የነዋሪነታቸውን ማረጋገጥ ያለቻሉ መራጮች በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲሳተፉ ህጉ አይፈቅደም። ነገር ግን የምርጫ ህጉ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሲከስቱ ማንነታቸውን በምስክሮች እንዲያረጋግጡ ይፈቅዳል። በዚሁ መሰረት በምርጫ ጣቢያዎች የማንነት እና/ወይም የነዋሪነት ማረጋገጫ ያላቀረቡ መራጮች አስምስከረው ድምጽ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።

5. የምርጫ ህጉ የተመዘገቡ እና ለመምረጥ የነዋሪነት እና የማንነት ማረጋገጫ ማቅረብ የቻሉ መራጮች ድምጽ የመስጠት መብት እንዳላቸው የደነገጋል ። ከዚህ ጋር በተገናኘ በ 10 (83%) የምርጫ ጣቢያዎች የነዋሪነት እና የማንነት ማረጋገጫ ያቀረብ መራጮች ድምጻቸውን እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል። በተቀሩት2 (16%) ጣቢያዎች ደግሞ አንዳንድ ግለሰቦች መታወቂያ ቢያቀርቡም ያቀረቧቸው መታወቂያዎች ከስድስት ወር ባነሰ ጊዜ የተሰጡ በመሆናቸው እንዳይመዘገቡ እና እንዳይመርጡ ተደርጓል።

6. የምርጫ ህጉ መራጮች ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት ጣታቸው በማይለቅ የጣት ቀለም እንዲቀልም ያስገድዳል። በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች በሁሉም መራጮች ጣት ላይ የማይለቅ እንደተደረገባቸው ሪፖርት ተደርገዋል።

7. በምርጫ አዋጁ መሰረት የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የመራጮች ስም በመራጮች መዝገብ ውስጥ መገኘቱን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። በዚሁ መሰረት በሁሉም 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የመረጡ መራጮች በሙሉ ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ተገኝቷል።

8. የምርጫ ህጉ የምርጫ አስፈጻሚወች ሁሉንም የድምጽ መስጫ ወርቀቶች ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት ማህተም እንዲያደርጉ ያስገድዳል። በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች፣ የምርጫ አስፈጻሚወች በሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ማህተም ማድረጋቸውን የኅብረቱ ታዛቢውች ሪፖርት አድርገዋል።

9. በ12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ምስጢራዊነት ቀኑን ሙሉ ተከብሮ ነበር።

10. በ12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የአካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን ያልሆኑ መራጮች እርዳታ/ድጋፍ አልተደረገላቸውም።

11. በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ጊዜ፣ በ12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ያልተፈቀደላቸው ሰዎች ውስጥ አልተገኙም።

12. በ 12 (100 %) የምርጫ ጣቢያዎች በአጠቃላይ የማስፈራራት እና እንግልት በተለይም ሴት መራጮችን፣ የፓርቲ ወኪሎችን፤ ታዛቢዎችን እና የምርጫ አስፈጻሚዎችን የጥቃት ሰለባዎች አልነበሩም።

13. በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ አንደም ገዜ አልተቋረጠም።

14. የምርጫ አዋጁ የምርጫ ጣቢያዎች የመዝጊያ ሰአት ከቀኑ 12:00 ሰዓት መሆኑን ይደነግጋል። በ12(100 % ) ጣቢያዎች በሕጉ በተደነገገው መሰረት መዘጋታቸውን ታዛቢውች ሪፖርት አድርገዋል።

## የድምጽ ቆጠራ

1. በድምጽ ቆጠራ ወቅት በ12 (100 %) በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የነበሩ ታዛቢዎች ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጡ አልተጠየቁም።

2. የድምፅ ቆጠራ በምርጫው ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መከናወን አለበት።. የድምጽ ቆጠራው በድምጽ መስጫ ቀን በ12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች ተካሂዷል።

3. የድምጽ ቆጠራው በ 12 (100 %) የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች አልተቋረጠም ነበር።

4. በ12(100%) የምርጫ ጣቢያዎች በቆጠራው ሂደት ምንም አይነት ጣልቃገብነት፣ ትንኮሳ እና/ወይም ማስፈራራት አልነበረም።

5. በ 12 (100%) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ የነበሩ ሃላፊወች በድምጽ ቆጠራው ወቅት የምርጫ ወረቀቶቹን በግልፅ አሳይተዋል።

6. በ 12 (100 %) የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ወጥ የሆኑ መስፈርቶችን መተግበራቸውን የትዝብት ሪፖርቶች ያሳያሉ።

7. ምንም እንኳ ታዛቢዎች ዜጎች ቅሬታቸውን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሲገልጹ ሰምተናል ቢሉም በምርጫ ጣቢያ ለተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የቀረቡ መደበኛ ቅሬታዎች አልነበሩም ።

# ሶማሌ ክልል (ጅግጅጋ ምርጫ ክልል)

ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ሶማሌ ክልል የጅግጅጋ ምርጫ ክልል በ8 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ተሰማርተው ቀኑን ሙሉ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ሲታዘቡ በነበሩ 8 ታዛቢዎች አማካኝነት በተሰበሰበው የትዝብት መረጃ ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ሲሆን ኀብረቱታዛቢዎችን ለማስማራት እመቺነትን መሰረት ያደርገ የስምሪት ዘዴን (Convenient deployment method) በመጠቀም ነበር። ይህ ሪፖርት የምርጫ አስፈጻሚዎች ወደ ምርጫ ጣቢያዎች መድረስ፤ የምርጫ ጣቢያዎች ዝግጅትን፤ የድምጽ መሰጫ ጣቢያ አከፋፈትን ፤ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን ፣የድምጽ መሰጫ ጣቢያ መዘጋት፣ ቆጠራ እና የውጤት ማዳመርን እንዲሁም በድምጽ መስጫ ጣቢያ ውጤት መለጠፍን/ የሚመለከቱ መረጃዎችን አካትተቷል።

## ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መድረስን በተመለከተ

1. የምርጫ አስፈጻሚዎች ከንጋቱ 12፡00 ሰዓት ጣቢያዎቹ ከመከፈታቸው አስቀድሞ በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት ይጠበቅባቸዋል። በሁሉም(8) ጣቢያዎች የምርጫ አስፈጻሚዎች ከማለዳው 11፡30 በምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተዋል።

2. በሁሉም(8) የምርጫ ጣቢያዎች፣ የተሰማሩ የኅብረት ለምርጫ ታዛቢዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን ለመታዘብ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ተገኝተው እንዲታዘቡ ተፈቅዶላቸዋል።

3. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 12፡00 ሰአት መከፈት አለባቸው። የኅብረቱ ታዛቢዎች ከማለዳው 12 ሰዓት በሁሉም(8) የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ መጀመሩን አመልክተዋል።

4. የምርጫ ህጉ በወታደራዊ ካምፖች፣ በግል መኖሪያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ የኀይማኖት ተቋማት ህንጻዎች፣ የጤና ተቋማት፣ የመዝናኛ ማዕከላት እና የፖለቲካ ፓርቲ ጽ/ቤቶች ውሰጥ የምርጫ ጣቢያዎችን ማቋቋም ይከለክላል። በዚህ መሠረት የኅብረቱ ታዛቢዎች በታዘቧቸው በሁሉም(8) የምርጫ ጣቢያዎች በምርጫ ሕጉ ባልተከለከሉ ቦታዎች ፤መቋቋማቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. በምርጫ ቀን የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራትን በተመለከተ፣ የምርጫ ህጉ በምርጫ ጣቢያው ውስጥም ሆነ ከምርጫ ጣቢያ 200 ሜትር ርቀት ላይ ማንኛውንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎችን በግልፅ ይከለክላል። ከዚህ ጋር በተያያዝ በ7 የምርጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች አልተካሄዱም ። ነገር ግን "ጅ 09 ምርጫ ጣቢያ ዞን-3/ሐ" በተባለ አንድ የምርጫ ጣቢያ በ20 ሜትር ውስጥ የትውስኑ ግልሰቦች ምራጮች የብልጽግና ፓርቲንን እንዲመርጡ ምራጮቸን ሲቀስቅሱ እንደነበር ታዛቢወች ሪፖርት አድርገዋል። በተጨማሪም ከሶማሌ ክልል የተመለመሉ የምርጫ አስፈጻሚውች ሊመረጡ ወደጣቢያው የሚምጡ መራጮችነ በድምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ ካሉት ከ3 እስከ 9 ያሉትን ዕጩዎች እንዲመርጡ ሲነግሯቸው እንደነበር ታዛቢውች ሪፖርት አድርገዋል።

## የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ዝግጅት

1. የምርጫ ጣቢያዎች የሚቋቋሙበት ቦታ ጣቢያዎቹ ለዜጎች ያላቸውን ተደራሽነት ዜጎች በምርጫ ሂደቱ በሚኖራቸው ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ አለው። በዚህ ረግድ 6 የምርጫ ጣቢያዎች በድንኳን ውስጥ ሲቋቋሙ 2 ጣቢያዎች ደግሞ በህንፃዎች መቋቋማቸውን በኅብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት ተደርጓል።

2. መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሐይ ወረፋ ለመከላከል ከምርጫ ጣቢያዎች ውጭ መጠለያ መኖሩ በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት አስፈላጊ ንገር ነው። 6 የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከፀሃይ እና ከዝናብ የሚከላከሉ መጠለያዎች የነበሯቸው ሲሆን ፤ 2 የምርጫ ጣቢያዎች መራጮችን ከዝናብ እና ከፀሀይ የሚከላከሉ መጠለያዎች አልነበሯቸውም።

3. በምርጫ ጣቢያዎች አደረጃጀት ሌላው ወሳኝ ጉዳይ አረጋውያን፣ ነፍሰ ጡር ሴቶቸን፤ ህጻናትን አስከተለው ለሚመጡ እናቶች እና አካል ጉዳተኞችን ለመሳሰሉ የመንቀሳቀስ ችግር ላለባቸው መራጮች የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት ጋር የተያያዘ ሲሆን 5 የምርጫ ጣቢያዎች ክዚህ በላይ ለተዘረዘሩት የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ የነበሩ ሲሆን 3ቱ ጣቢዎች ደግሞ ተደራሽ አልነበሩም።

4. በምርጫ ህጉ መሰረት የምርጫ ጣቢያዎችን በተሟላ መንገድ ለማዘጋጀት የምርጫ ቁሳቁሶች በ ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተሟልተው መገኘት አስፈላጊ ጉዳይ ነው። የደምጽ መስጫ ወረቀቶች፣ የመራጮች መዝገብ፣ኦፊሴላዊ ምርጫ ቦርድ ማህተም ፣ የውጤት እና የእርቅ ፎርም፣ የማይለቅ የጣት ቀለም፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን፣ የድምጽ መስጫ ሳጥን እና የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች በምርጫ ጣቢያዎች ተሟልተው ይገኙ እንደሆነ የተጠየቁት ኅብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በታዘቧቸው 8 ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ቅጽ ከ ጎደለበት “ጅ 06 ምርጫ ጣቢያ 02” ከሚባል የምርጫ ጣቢያ በስተቀር የምርጫ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኝታቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ መሆናቸውን እንዲያሳይ የምርጫ ህጉ ያስገድዳል። በሁሉም (8) የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የምርጫው ሂደት ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫ ሳጥኖች ባዶ ምሆናችወን አሳይተዋል።

6. የምርጫ ህጉ ቢያንስ 3 የምርጫ አስፈጻሚዎች በየምርጫ ጣቢያዎቹ መገኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል። ኅብረቱ ያሰማራቸው ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች በአማካይ 4 የምርጫ አስፈጻሚዎች መገኘታቸውን ከነዚህም መካከል በአማካይ 2 የምርጫ አስፈጻሚዎች ሴቶች እንደነበሩ ሪፖርት አድርገዋል። የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎችን የሥርዓተ-ፆታ ውክልናን በተመለከተ በ2 የምርጫ ጣቢያዎች ሃላፊዎቹ ሴቶች ሲሆኑ በቀሪዎቹ 6 የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎቹ ወንዶች እንደነበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት አድርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ ኅብረቱ ታዛቢዎችን ባሰማራባቸው በሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች አንድም አካል ጉዳተኛ የምርጫ አስፈጻሚ አለመኖሩን አረጋግጠዋል።

7. የምርጫ ህጉ ሶስት አባላት ያሉት የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን በምርጫ ጣቢያዎች እንደሚያቋቁም ይደነግጋል። በዚሁ መሰረት *ጅ 06 ምርጫ ጣቢያ 02* እና *ጅ 04 ምርጫ ጣቢያ 03* በተባሉ የምርጫ ጣቢያዎች የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የተቋቋሙ ሲሆን በሌሎች ጣቢያዎች የቅሬታ ኮሚቴዎቹ አልተቋቋሙም።

8. የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች በምርጫ ጣቢያዎች መገኝታቸውን በተመለከተ፣ በ6 የምርጫ ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ውኪሎች መገኘታቸውን ታዛቢዎች የገለጹ ሲሆን በ2 ጣቢያዎች የፖለቲካ ፓርቲ ወኪሎች አልተገኙም ነበር።

## የድምጽ አሰጣጥ ሂደት

1. በሁሉም (8) ትዝብት በተደረገባቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ታዛቢዎች ጣቢያዎቹን ለቀው እንዲወጡ አለመጠየቃቸውን ሪፖርት አድርገዋል።

2. በ8 የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊዎች ለአካል ጉዳተኞችን አረጋውያን፣ ለአቅመ ደካሞች፣ ለእርጉዝ ሴቶች፣ እና ህጻናትን ለያዙ ወላጆች ቅድሚያ የሰጧቸው መሆኑን ታዛቢዎች ገልጸዋል።

3. ትዝብት በተደረገባቸው ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች አካል ጉዳተኞች በመረጡት የግል ረዳት እግዛ እንዲደረግላቸው ተፈቅዶላቸው ነበር።

4. የምርጫ ህጉ መራጮች ለመመዝገብ እና/ወይም ድምጽ ለመስጠት የነዋሪነት እና/ወይም የማንነት ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ያስገድዳል። ማንነታቸውን እና የነዋሪነታችወን ማረጋገጥ ያለቻሉ መራጮች በድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ እንዲሳተፉ ህጉ አይፈቅደም። ነገር ግን የምርጫ ህጉ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሲከስቱ ማንነታቸውን በምስክሮች እንዲያረጋግጡ ይፈቅዳል። በዚሁ መሰረት ምርጫ ጣቢያዎች የማንነት

ማረጋገጫ እና/ወይም የነዋሪነት ማረጋገጫ ያላቀረቡ መራጮች አስምስከረው ድምጽ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።

5. በምርጫ ህጉ መሰረት የተመዘገቡ እና ለመምረጥ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ማቅረብ የቻሉ መራጮች ድምጽ የመስጠት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። ከዚህ ጋር በተገናኘ በሁሉም(8) ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የሰነድ መስፈርቶችን ያሟሉ መራጮች ድምጻቸውን እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸዋል።
6. የምርጫ ህጉ መራጮች ድምጽ ከመስጠታቸው በፊት ጣታቸው በማይለቅ የጣት ቀለም እንዲቀልም ያስገድዳል። ትዝብት በተደረገባቸው ሁሉም (8) የምርጫ ጣቢያዎች በሁሉም የመራጮች ጣት ላይ የማይለቅ ቀለም እንደተደረገባቸው ሪፖርት ተደርጓል።
7. በምርጫ አዋጁ መሰረት የምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች የመራጮች ስም በመራጭ መዝገብ ውስጥ መገኘቱን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። በዚሁ መሰረት በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የመረጡ መራጮች በመሉ ስማቸው በመራጮች መዝገብ ላይ ተገኝቷል።
8. የምርጫ ህጉ የምርጫ አስፈጻሚወች ለመራጮች ከመስጠታቸው በፊት በሁሉም የድምጽ መስጫ ወርቀቶች ማህተም እንዲያደርጉ ያስገድዳል። ትዝብት በተደረገባቸው በ8 የምርጫ ጣቢያዎች፣ የምርጫ አስፈጻሚወች በሁሉም የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ላይ ማህተም ማድረጋቸውን ታዛቢውች ታዝበዋል።
9. በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ምስጢራዊነት ቀኑን ሙሉ ተከብሮ ነበር።
10. በ3 የምርጫ ጣቢያዎች የአካል ጉዳተኞ እና አረጋውያን ያልሆኑ መራጮች እርዳታ/ድጋፍ ተደርጎላችዋል ።
11. በድምጽ አሰጣጥ ሂደት በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው የመረጫ ጣቢያዎች ያልተፈቀደላቸው ሰዎች በምርጫ ጣቢያዎቹ ውስጥ አልተገኙም።
12. በበሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች በአጠቃላይ የማስፈራራት እና እንግልት በተለይ ሴት መራጮች፣ የፓርቲ ወኪሎች፤ ታዛቢዎች እና የምርጫ አስፈጻሚዎች የጥቃት ሰለባዎች አልነበሩም።
13. ሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ አልተቋረጠም።
14. የምርጫ አዋጁ የምርጫ ጣቢያዎች የመዝጊያ ሰአት ከቀኑ 12:00 ሰዓት መሆኑን ይደነግጋል። 8 ቱም ትዝብት የተደረገባቸው የመረጫ ጣቢያዎች በሕጉ በተደነገገው መሰረት መዘጋታቸውን ታዛቢወች ሪፖርት አአድርገዋል።

## የድምጽ ቆጠራ

1. በድምጽ ቆጠራ ወቅት በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የነበሩ ታዛቢዎች ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጡ አልተጠየቁም።
2. የድምፅ ቆጠራ በምርጫው ቀን በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ መከናወን አለበት።. የድምጽ ቆጠራው በድምጽ መስጫ ቀን በሁሉም(8) ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች ተካሂዷል።
3. የድምጽ ቆጠራው ሂደት በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች አልተቋረጠም ነበር።

4. በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች በቆጠራው ሂደት ምንም አይነት ጣልቃገብነት፣ ትንኮሳ እና/ወይም ማስፈራራት አልነበረም።

5. በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊወች በድምጽ ቆጠራው ወቅት መስጫ ምርጫ ወረቀቶቹን በግልፅ አሳይተዋል።

6. በሁሉም ትዝብት በተደረገባቸው ጣቢያዎች የምርጫ ጣቢያ ሃላፊወች ዋጋ ያላቸውን እና ዋጋ የሌላቸውን የድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመወሰን ወጥንት ያላቸው መስፈርቶችን መተግበራቸውን የትዝብት ሪፖርቶች ያሳያሉ።

7. ምንም እንኳ ታዛቢዎች ቅሬታቸውን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ዜጎች ሲገልጹ ሰምተናል ቢሉም በምርጫ ጣቢያ ለተቋቋሙ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች የቀረቡ መደበኛ ቅሬታዎች አልነበሩም ።

***

**For media inquiries please contact:**

Eyuel Zelealem
***Coalition of Ethiopian Civil Society Organizations for Elections (CECOE)***
Tel. +251 91 240 6232 / +251 11 811 1455
Email: Info@cecoe.org

Learn more about CECOE at www.cecoe.org
or on social media on Facebook at www.facebook.com/CECOEeth or on Twitter @CECOEeth